# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

## ለሰፊው ሕዝብ
(መዛይሮ፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣)
መብትና ጥቅም
## የሚታገል ጋዜጣ


ጥቅምት 12/1989 ዓ.ም.
ቁጥር 1/89

## አበራ የማነአብ

ከወጣትነት ዕድሜው ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ክብር ዕድገትና ብልጽግና ያለመታከት ሲታገል የቆየው አበራ የማነአብ በወያኔ/ኢህአዴግ እሥር ቤት የመከራ ሕይወት ማግፋት ከጀመረ እነሆ ዓመታት ተቆጥረዋል:: ይህ ስመጥሩና ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጅ ኢትዮጵያን ለማበተን፣ሕዝቦቿን ለመከፋፈልና ለማዋረድ በከሀዲዎች የተጠነሰሰውን ሴራ ያለአንዳች ማመንታት በማጋለጡና በመዋጋቱ በዘመኑ የኢትዮጵያ ገዢዎች ለጥቃት ተዳርጓል::

በታህሣሥ 1986 በአዲስ አበባ ላይ በተደረገው የሰላምና የእርቅ ጉባኤ ለመሳተፍ በሕጋዊ መንገድ ከስደት የተመለሰው አበራ የማነአብ ከ15 ዓመታት በላይ የተለያትን የሀገሩን መሬት ገና ከመርገጡ ከቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ በኢህአዴግ የፀጥታ ሀይሎች ተጠልፎ እስከዛሬ በእስር ላይ ይገኛል::

ጦርነትን በማነሳሳትና መንግስትን በመድፈር ወንጀል የወያኔ አቃቤ ሕግ የመሠረተበት ክስ በማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ወንጀል ችሎት ሲታይ ከቆየ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ክሱን ውድቅ በማድረግ ተከሳሹ በነፃ እንዲለቀቅ መወሰኑ ይታወቃል:: ሆኖም፣የሕግን የበላይነት ለመስበርና ፍትህን ለማዛባት የተቋቋመውና የወቅቱን አምባገነኖች ለማገልገል የተዋቀረው የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማንአለብኝነት በመሻር ተግባራዊ እንዳይሆን አግዷል:: ይህንን ሕገወጥ አድራጎት ለመሸፋፈንም "በቀይ ሽብር ወንጀል ይፈለጋል ብሎ" በመንግስት መሪዎች አንደበት ሳይቀር አስነግሯል:: ሆኖም በዚህ ጉዳይ ክስ መስርቶ አበራ የማነአብን ለፍርድ ለማቅረብ እስካሁን አልተቻለውም:: ምክንያቱም፣ ይህ ልዩ ዐቃቤ ሕግ የተሰኘው የወንጀለኞች መሣሪያ ተጠቃሹንም ሆነ በተመሣሣይ ምክንያት ያገታቸውን በሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን በአደባባይ ተሟግቶ ለመርታት የሚያስችለው እውነት ስለሌለው ነው:: ወያኔ/ኢህአዴግ፣ይህንን በተመለከተ የሚከተለው ጭፍን ሕገወጥነት አልበቃ ብሎት "አበራ እስረኞችን ለማስመለጥ አስተባብሯል" በሚል የሀሰት ውንጀላ ተጨማሪ የማስቀየት ድርጊቶችን ሲፈጽምበት መቆየቱን ለመረዳት ተችሏል::

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) የአመራር አባል የሆነው አበራ የማነአብ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት እንዲፈታና በኋላም የቀረበበትን የፈጠራ ክስ በግልፅ ችሎት እንዲከላከል ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ለአቶ መለስ ዜናዊ ወታደራዊ መንግስት በተደጋጋሚ የቀረቡት በርካታ ጥያቄዎች እስከዛሬ ምላሽ አላገኙም:: ይህም የኢህአዴግ የተለመደ የአሰራር ዘይቤ በመሆኑ እምብዛም ባያስገርምም ሁኔታውን እንደገና ማገለፁ አስፈላጊ ሆኗል::

የአበራ የማነአብን ጉዳይ ሰላምና ፍትህ ወዳድ ኢትዮጵያዊያን፣ የአለም አቀፍ ሕብረተሰብ አባላትና እንዲሁም መንግስታት በቅርብ እየተከታተሉ የሚቻላቸውን ግፊት እንዲያደርጉ ጥሪ እናቀርባለን::

ኢትዮጵያ በነፃነትና በአንድነት ትኑር!
ፍትሕ ለአበራ የማነአብና በግፍ ለታሰሩ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ!